# ተዘጋጅ ካሁኑ

ጌታው አቶ አብይ ፣ ጠ/ ሚኒስትሩ
ስልጣን ሲረከቡ ፣ አገርን ሊመሩ
እንደሰማናቸው ፣ ለዓለም ሲናገሩ
የከረፋው ጠረን ፣ ተገፎ ካየሩ
ሃሴትና ደስታ ፣ ነበር በሀገሩ
    እንኳንስ የሰው ልጅ ፣ ሳር ቅጠሉ ምድሩ
    ያዝልቅ ያዝልቅ ፣ ብሏል እንዳጀማመሩ ።

ኢትዮጵያዬ የሚል ፣ ጆሮ የናፈቀውን
የአንድነት መሰረት ፣ ዋልታ ምሶሶውን
ለወያኔ ሹምባሽ ፣ ቅዠት የሆነውን
የጥቁር አርአያ ፣ አርበኛ ጀግናውን
የጣሊያን ሶላቶን ፣ ያንበረከከውን
ኢትዮጵያን በዓለም ፣ ስሟን ያስጠራውን
እምዬ ሚኒሊክ ፣ የአድዋ አንበሳውን
ሲወደስ ሰማነው ፣ የአፍሪቃ አውራውን ።

ግና ምን ያደርጋል ፣ እነ ስም አይጠሬ
አገሩን ያጦዙት ፣ በጥላቻ ወሬ
ወያኔ የሚባሉት ፣ የሰሜኑ ትግሬ
ብዙ ሃብት ስላለኝ ፣ በዝርፊያ ከብሬ
ትግራይን ከልዬ ፣ ድንበሬን አጥሬ
እንዳታንሰራራ ፣ ኢትዮጵያን ቀብሬ
እኖራለሁ ያለው ፣ አጋሰሱ በሬ
ህልማቸው ተዳፍኖ ፣ ሆነባቸው ወሬ ።

በጥላቻ ስሜት ፣ ነፍዘው የሰከሩ
የደደቢት ደደብ ፣ እናቶ ደፋሩ
አንገት አንደደፉ ፣ አንዳቀረቀሩ
እርር ድብን ብለው ፣ ከሰሉና አረሩ
በተቀመጡበት ፣ ውሃ ሆነው ቀሩ ።

ጊዜ ዘመም ብሎ ፣ ቢያጋድል ሚዛኑ
እርር ድብን ብለው ፣ ቢጠናም ሃዘኑ
ባስመስሎ ማደር ፣ እጅግ የተካኑ
የማያንቀላፉ ፣ ተባይ ስለሆኑ
        መቀሌ ከትመው ፣ ማድባት በየቀኑ
        በስውር ስብሰባ ፣ ሴራ መጎንጎኑ
        አድብቶ ለመጣል ፣ ዘዴ እየወጠኑ
        እንዳለ ተረዳ ፣ ተዘጋጅ ካሁኑ
        ትላትል አያጣም ፣ ሾላ በድፍኑ
        በተለይ ወያኔ ፣ የተንኮል ካህኑ ።

ታዛቢው

April 3, 2018